# ሰው ሲጠፋ…

ይዋል፣ ይደር ስንል፣ ከጉን እየቀረ፣
‘ትንሽ ይቆይ!’ ስንል፣ እየተከመረ፣
ምን ያልተባለ አለ፣ ምን ያልተነገረ?
ምን ያልተሠራ አለ፣ ምን ያልተሞከረ?

በማር ከንፈራቸው ሰው የሚደልሉ፣
‘ተዉ እንጂ!’ ሲሏቸው በጅ የማይሉ
እያወናበዱ ብዙ ’ሚያታልሉ
ሓሳውያን መሲሓን በየቦታው አሉ

ማንም ሳይነካካው፣ ሳይከፋፍተው
እጁን አስገብቶ ሳይፈተፍተው
እንደተከደነ እንዲበስልልን
አንድም ሰው ሳያየው ይቀመጥልን…

እናስተምር ብለው የተደናቆሩ
ለመምራት ተነስተው ከኋላ የቀሩ
ተከድኖ ይቀመጥ ሳይታይ ምስጢሩ
ተው አትነካኩ፣ አትጐራጉሩ…

ሓሰትን ከእውነት እየቀላቀሉ
መጥፎውን ሸፋፍነው ደግ እያስመሰሉ
በፍልስፍናቸው ዓለም የበከሉ
ብዙ ተንኰለኞች ከብረው ይኖራሉ

አዋቂው ወደፊት ደፍሮ እንዳይወጣ
ልባሙ ወደፊት ተራምዶ እንዳይመጣ
ምላሳቸው እሳት፣ በርበሬ፣ ምጥሚጣ
ስልጣንም አላቸው፣ ገርፎ የሚቀጣ

ስንቱ ተታለለ፣ ስንቱ ሰው ተሞኘ
በማርክስ፣ በሌኒን እየተመኘኘ፣
በርእዮተ ዓለም እየተጐዳኘ፣
ዋናው ችግራችን ሰው ሆኖ ተገኘ!

አንዳንዱም ዐዋቂ ዝምተኛ ሰው
ሌላም ምላሰኛ “አለሁ!” የሚለው
ቀፎ ጭንቅላቱን የሚያስመዝነው
ለእውነት የቆመ በመጥፋቱ ነው!

ቀኑ ይርዘም እንጂ እውነቱስ ይወጣል
ሓሰትን ከመካብ ሓቅ እንጂ ይበልጣል
ምስጢሩም እንዳለ ከዚያው ይቀመጣል

ባለ ዘንጉም ጌታ በድንገት ይመጣል። ገ/ኢ. ጐርፉ።